**ORIGINAL ARTICLE**

# A Feminist Reading in Ethiopian Philosophy as Portrayed in Treatises of Zara-Yaqob and Wolde-Hiwot

**Dawit Girma [1]**

## *Abstract*

*This study investigates the perspectives of medieval Ethiopian philosophers, Zara-Yaqob and Wolde-Hiwot concerning women through the lens of feminist criticism. Referred to as 'The Golden Age of Ethiopian Literature', the medieval era in Ethiopian history witnessed the creation of numerous manuscripts covering a wide array of subjects, including the humanities and natural sciences. During this period, a diverse range of books featuring philosophical musings, Qine (Ethiopian poetic form), and other literary works were produced both original compositions and adopted translations. The research is temporally delimited to the 17th century and concentrates on the philosophical writings of the first Ethiopian philosophers from the town of Enfranz/Gondar. Employing a descriptive approach, the study scrutinizes how these philosophers depict women in their works, utilizing a feminist perspective as its theoretical framework. Feminism, concerned with promoting women's equal engagement and empowerment across social, economic, and political spheres, underpins the analytical lens applied in this investigation. Feminism identifies and challenges the ways in which women are marginalized, discriminated against, and oppressed. The impetus behind this study is to explore the historical context and understanding of feminism in Ethiopia through the logical reasoning of indigenous philosophers. Prior to the emergence of the feminist movement, which has gained momentum in later years, these thinkers delved into issues of gender equality during a time when the international community was predominantly patriarchal. The philosophers espoused positive views on various aspects of equality, including decision-making within marital life, property rights, division of labor, rejection of polygamy, and the freedoms that girls should have regarding their sexual lives and menstruation cycles. Similar to Zara-Yaqob, Wolde-Hiwot also shares feminist perspectives; however, unlike his mentor, he portrayed women as weak and emotional, aligning with the views of many pro male advocates. While his initial stance on gender equality paralleled that of Zara-Yaqob, it did not persist until the end. This study emphasizes that Ethiopian philosophers accorded significant value to femininity, particularly when compared to their contemporaries who espoused misogynistic and patriarchal influences, and predating the onset of feminist movements; the treatises of Zara-Yaqob and Wolde-Hiwot provide insight into this perspective.*

**Keywords**: *Ethiopian Philosophy; Feminism; Medieval Age; Traditional fender role; Feminist philosophy*

## አጠቃሎ

ይህ ጥናት በመካከለኛው የታሪክ ዘመን የተከሰቱትን ሁለት የኢትዮጵያ ፈላስፋዎችን ዘርአያዕቆብ እና ወልደሕይወት “ሴት”ን እንዴት እንደተገነዘቧት ከእንስታዊ ሥነጽሑፋዊ ሂስ አንጻር ይመለከታል። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ መካከለኛው ዘመን “ወርቃማው የሥነጽሑፍ ዘመን” በመባል ይታወቃል ። በዘመኑ ፋይዳ ብዙ ሀገር በቀልና ትርጉም የሥነሰብዕ እና የተፈጥሮ ሳይንስ ይዘት ያላቸው መጻሕፍት ተደርሰዋል ። በመካከለኛው ዘመን ፍልስፍናዊ ይዘት ያላቸው እሳቤዎች፣ ቅኔዎችና መጻሕፍት ተጽፈዋል፤ ከፊል ኢትዮጵያዊ ሆነው ተወርሰዋል ። ጥናቱ 17ኛውን ክፍለዘመን የጊዜ ገደብ አርጎ በዘመኑ በምድረ እንፍራዝ፣ ጎንደር ይፈላሰፉ በነበሩ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ፈላስፋ ዘርአያዕቆብና ደቀ መዝሙሩ ወልደሕይወት በጻፏቸው የፍልስፍና ድርሳናት/ሐተታዎች የሴትነትን ውክልና

1. Debre Birhan University, Lecturer of English Literature
Email: dawitzion2000@gmail.com

እንስታዊነትን (Feminism) እንደንድፈሃሳባዊ መቀንበቢያ በመጠቀም በገላጭ ሥነዘዴ ሰነዶችን ተንትኗል ። የእንስታዊነት ንድፈሃሳቡም በሴቶች የማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አቅም መጎልበትና እኩላዊ ሱታፌ ላይ አተኩሯል ። ሴቶች ዝቅ የሚደረጉባቸውን፣ የሚገለሉባቸውንና የሚበዘበዙባቸውን መንገዶች በመለየት ለመቃወም ይሞክራሉ ። ይህን ጥናት ለማካሄድ ከአነሳሽ ምክንያቶች አንደኛው፣ በሀገራችን የነበረው የሴትነት አረዳድ ምን ይዞታና ታሪካዊ ዳራ እንዳለው በሀገራችን ፈላስፎች አመክንዮ መሠረት ማየት ሲሆን፣ በተለይ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በአባዊ (Patriarchal) ሥርዓት ስር በነበረበትና ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እየዳበረ ከመጣው እንስታዊ ንቅናቄ አስቀድሞ አሰላሳዮቹ ስለሴት ልጅ እኩልነት መርምረዋል ። ፈላስፋዎቹ በጋብቻ ሕይወት፣ በንብረት መዝገብ፣ በአብሮነት ኑሮ፣ በስራ ክፍፍል፣ በጊዜ ሩካቤና በወር አበባ፣ አንድ ለአንድ ስለመወሰን አዎንታዊ እይታን አንጸባርቀዋል ። ወልደሕይወትም ፍትሃዊ የነገረ ጾታ እሳቤው ከመምህሩ ጋር መሳ ለመሳ ቢሄድም ቅሉ፣ በተጻራሪው ሴትን ደካማና ስሜታዊ በማድረግ ከብዙኃኑ አፍቃሬ ወንድ አቀንቃኞች ጋር በአንጻሩ ይዛመዳል ። ሴት ከወንድ እኩል መሆኗን ያብራራበት እሳቤው እንደመምህሩ እስከመጨረሻው አብሮት አይዘልቅም ። በምዕራቡ ዓለም የኢትዮጵያውያኑ ፈላስፎች ዘመን ተጋሪ የሆኑ ፈላስፋዎችና አሳቢዎች በአባዊ ተጽዕኖ ስር በወደቁበት ወቅት፣ አፍቃሬ ሴት ንቅናቄዎች ከመደርጀታቸው ምዕተ ዓመታት በፊት የኢትዮጵያ ጽሑፋዊ ፍልስፍና ለሴትነት ዋጋ ሰጥቶ እንደነበር በሐተታ ዘርአ ያዕቆብና በሐተታ ወልደሕይወት ማሳያነት መደምደም ይቻላል።

**ቁልፍ ቃላት፡ –** የኢትዮጵያ ፍልስፍና፣ እንስታዊነት፣ የመካከለኛው ታሪክ ዘመን፣ ዘልማዳዊ የጾታ ሚና፣ እንስታዊ ፍልስፍና

## መግቢያ

ከክፍላተ ዘመናት በፊት አንስቶ አያሌ ጥንታዊ የብራና መጻሕፍት በሀገራችን ተደርሰዋል፤ መጻሕፍቱ ደግሞ በተለያዩ የእውቀት ዘርፎች የተሞሉ ናቸው። መጻሕፍቱ ጥልቀት ያላቸው ጥበባትን የያዙ ቢሆንም፣ በዘርፉ ይህ ነው የሚባል ጥናት አልተደረገባቸውም። ሙከራዎች ቢኖሩም ከይዘታቸው ዘርፈ ብዙነትና ጥልቀት አንጻር በሚያረካ ደረጃ አልተፈተሹም። በተለይም የኢትዮጵያ ፍልስፍናና ፈላስፋዎቹ በሚገባ አልተጠኑም፤ ይልቁንም እንስታዊነት በፍልስፍና ድርሰቶች ላይ ትኩረት አልተነሳውም። ሴትነት በእንስታዊ ንድፈሃሳብ ማዕቀፍነት ከደራስያኑ፣ ከተደራስያኑ ብሎም ከማኅበረሰባዊ አተያይና አቀባበል አንጻር የተመራማሪያኑን ትኩረት ስቦ በአንክሮ ማለት ይቻላል። በመሆኑም በዚህ ዘርፍ ያሉ ክፍተቶችን ለመሙላት ግብን ከማድረግ አኳያ ይህ ጥናት ተካሂዷል። ከዚህ ተጠየቅ በመነሳት ከግእዝ የፍልስፍና ድርሳናት ውስጥ ሐተታ ዘርአ ያዕቆብና ሐተታ ወልደ ሕይወትን ከእንስታዊነት ንድፈሃሳብ አንጻር ትንታኔ የሚሰጥባቸው መረጃዎች ናቸው ። በአጠቃላይ ይህ ጥናት የሁለቱን ኢትዮጵያውያንን ፈላስፎችን ሴትኛ ምልከታ በስፋት ይዳስሳል ። ሁለቱ ፈላስፋዎች ሴትን ልጅ እንዴት ነው የተረዷት? ሴትነትን በተመለከተ የኢትዮጵያ ፍልስፍና ምን መልክ አለው? በኢትዮጵያ ፍልስፍና ላይ ደራስያኑ ወንዶች በሆኑበት ሁኔታ ሴትን እንዴት ስለዋታል? የነገረ ጾታ አረዳድ ለኢትዮጵያ የሚኖረው ፋይዳ ምንድነው? የሚሉትና ሌሎች መሠረታዊ ጥያቄዎች ከሥነ ጾታ አንጻር ተዳሰዋል።

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ሐተታ ዘርአ ያዕቆብና ሐተታ ወልደ ሕይወት በተሰኙት የግእዝ የፍልስፍና ድርሳናት ላይ የሴትን አረዳድ ከእንስታዊነት ንድፈሃሳብ አንጻር መተንተን ነበር። ከዚህ በተጨማሪ የሀገራች የመካከለኛው ዘመን ማኅበረሰባዊ መስተጋብር ሴትነትን እንዴት ይዳኘው እንደነበር የመቃኘት፣ ዘርአ ያዕቆብና ወልደ ሕይወት በሴት አረዳድ ረገድ ልዩነት ያላቸው መሆኑን መፈተሽና፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ፍልስፍና ሴትን እንዴት እንደሚወክል የማየት ዝርዝር ዓላማም ነበረው ። ጥናቱ የስልጣኔ ክፍተትን ለመፈተሽና የእውቀት ልህቀትን ለሕዝብ ለማዳረስ ዓይነተኛ አስተዋጽኦ ያለው ሲሆን፣ ለእውቀት ዘርፍ ግንባታ፣ ለአእምሮ ብልጽግና፣ እንዲሁም ለምርምር እድገት ወሳኝ ፋይዳ ይኖረዋል። በኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ ሴትነት እንዴት እንደተገለጸና በሴትነት ላይ የነበረውን የቀደመ አረዳዳችን በባህላችን ምን እንደሚመስልም ጥናቱ ያሳያል። የጥናቱ ይዘታዊ ወሰን በተመረጡት ሁለት የፍልስፍና ስራዎች ላይ የኢትዮጵያውያንን ፈላስፎችን እንስታዊ ፍልስፍናን ማጥናት ይሆናል። የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ሐተታ ዘርአ ያዕቆብና ሐተታ ወልደ ሕይወት በተሰኙት የግእዝ የፍልስፍና ድርሳናት ላይ የሴትን አረዳድ ከእንስታዊነት ንድፈሃሳብ አንጻር መተንተን ነበር። ከዚህ በተጨማሪ የሀገራች የመካከለኛው ዘመን ማኅበረሰባዊ መስተጋብር ሴትነትን እንዴት ይዳኘው እንደነበር የመቃኘት፣ ዘርአ ያዕቆብና ወልደ ሕይወት በሴት አረዳድ ረገድ ልዩነት ያላቸው መሆኑን መፈተሽና፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ፍልስፍና ሴትን እንዴት እንደሚወክል የማየት ዝርዝር ዓላማም ነበረው ። ጥናቱ የስልጣኔ ክፍተትን ለመፈተሽና የእውቀት ልህቀትን ለሕዝብ ለማዳረስ ዓይነተኛ አስተዋጽኦ ያለው ሲሆን፣ ለእውቀት ዘርፍ ግንባታ፣ ለአእምሮ ብልጽግና፣ እንዲሁም ለምርምር እድገት ወሳኝ ፋይዳ ይኖረዋል። በኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ ሴትነት እንዴት እንደተገለጸና በሴትነት ላይ የነበረውን የቀደመ አረዳዳችን በባህላችን ምን እንደሚመስልም ጥናቱ ያሳያል። የጥናቱ ይዘታዊ ወሰን በተመረጡት ሁለት የፍልስፍና ስራዎች ላይ የኢትዮጵያውያንን ፈላስፎችን እንስታዊ ፍልስፍናን ማጥናት ይሆናል።

## እንስታዊ ሂስ (Feminist Criticism) እንደ ንድፈሃሳብ ማቀንቀኛ

በሴቶች ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አቅም መጎልበትና እኩላዊ ሱታፌ ላይ የሚያተኩረው የእንስታዊነት ንድፈሃሳብ የቅርብ ጊዜ ሁነት ሲሆን፣ ላለፉት ጥቂት አስርት ዓመታት ትልቅ ተጽዕኖ አሳርፏል። ሴቶች ተነጥለው ዝቅ

የሚደረጉባቸውን፣ የሚገለሉባቸውን፣ የሚበዘበዙባቸውን መንገዶችንም በመለየት ይቃወማሉ፡፡ እስከ 1960ዎቹ ድረስ እንስታዊነት እንደሥነጽሑፋዊ ንድፈሃሳብ ሆኖ ግዘፍ አልነሳም ነበር። ከዚያ በፊት የተናጠል የጽሑፍ ሥራዎች ስለሴቶች የእኩልነት ትግል ጭብጥን አንግበው ብቅ ብለዋል፡፡

የምዕራቡ እንስታዊውያን እንዲህ ብለው ይከራከራሉ፡፡ ምዕራቡ ዓለም አባዊ (patriarchy) ነው፡፡ በሁሉም የባህል መስተጋብሮች ሴቶች ጥገኛ/ዝቅተኛ ናቸው፤ በኃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በኪነጥበባዊ፡፡ ሴቶች የሰፈነውን የወንዶችን በላይነት እንዲቀበሉ ይገደዳሉ፡፡ ይህም ማለት የወንዶችን የበላይነትና ሴቶች ራሳቸውን/ጾታቸውን ዝቅ አድርገው እንዲመለከቱ ይደረግ ነበር፡፡ ሥነ ጾታ ማለትም፤ ወንዴነት (masculine) እና ሴቴነት (feminine) በባህል ተጽዕኖ ስር ሆኖ የተገነባ ነው፡፡ ሥነጽሑፉ በብዛት በወንዶች የተጻፈ ሲሆን፣ ሥነጽሑፎቹም አባዊ ርዕዮተ ዓለምን ደግፈው የተቀነበቡ ናቸው፡፡ በሥነጽሑፉ ውስጥም ሴቶች ሁለተኛ ደረጃ ሆነውና ጥገኛ ተደርገው ተስለዋል፡፡

እንስታውያን የሥነጽሑፍን[2] ፍትሃዊነት ከሴቶች እሴቶች አንጻር አትኩሮት ሰጥተው ይመለከቱታል፡፡ በዚህም ሁለት ዓይነት ዋና የአንስታይ ሂስ ተቋሞች[3] አሉ፡፡ አንደኛው የአሜሪካ/ብሪታንያ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የፈረንሳይ ነው፡፡ እንደአሜሪካ /ብሪታንያ ጽሑፎች በሴቶችና ስለሴቶች የተጻፉ መሆን አለባቸው፡፡ ሴቶች እንዴትና ለምን ይጽፋሉ? የሚለውና በሥነጽሑፍ ስራዎች እንዴት ተወክለዋል? የሚለው የዚህ ተቋም ትኩረት ነው፡፡ የፈረንሳዩ ሂስ ቡድን በሌላ መልኩ ቋንቋ ላይ ያተኩራል፤ የቋንቋ አጠቃቀም በምን ጾታ ተወክሏል? በወንዴ አገላለጽ የተቃኘ ነው? የወንድ የበላይነት ተንጸባርቆበታል? የሚለውን ይመለከታል፡፡

እንስታዊነት በሰፊ አውድ ሲበየን፣ ሥነጽሑፍና ሌሎች የባህል ተዋጽኦዎች የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ሥነልቦናዊ ኩነቶች ውስጥ መገለልና መረገጥን በአንክሮ ያጠናል[4]፡፡ እንደታይሰን አባባልነ በጽሑፍ የሚገለጸው "እሱ" የሚለው የወንድ ጾታ ተውላጠ ስም ሁለቱንም ጾታዎች እንዲወክል መደረጉ በእንስታውያን[5] ዘንድ አይደገፍም ፡፡ እንደሥነጽሑፋዊ ሂስ ሴቶች በጽሑፎች ላይ እንዴት እንደተሳሉ ያሄሳል፡፡ የሴቶችን ስሜታዊ፣ ጾታዊና ስነ ልቦናዊ ጥላቻን ይታገላል፡፡ ከ1970ዎቹ በፊት የእንስታዊነት ንቅናቄ ዋነኛ ትኩረት በሴቶች የደራሲነት ሚናና የሥነጽሑፍ ላይ ተወክሎት ነበር፡፡ ከዚያም ይበልጥ ውስብስብ ወደሆነ የፍሮይድና ላካንን እሳቤዎች ያማከለ የሥነ ጾታ ጽንሰ ሐሳብነት ተሸጋግሯል፡፡ እንስታዊነት ነገሮችን ከሴቶች መነጽር እንድንመለከት ይገፋፋል፡፡ ወንድ መር የሆነው ማኅበረሰብ ሴቶችን እንደ "ሌላ"6 ("Other") ይቆጥራቸዋል፡፡ ሴቶችን ከስኬት ሊያርቀቸው ወይም እንቅፋት ሊሆንባቸው የሚችሉትን ሁኔታዎች ይቃወማል፡፡ እንስታዊነት በጠቅላላው ምሁራዊና ፖለቲካዊ የሴቶች ንቅናቄ ነው፡፡

በዘልማዳዊው የጾታዎች ሚና ልየታ ለሴቶች የተለገሳቸው ቦታ በአድሎ የታጀበ ነው፡፡ ሴቶች እንደሁለተኛ ትርፍ አካላት ይቆጠራሉ እንጂ የሚገባቸውን ትክክለኛ ሰብአዊ ቦታ አላገኙም፡፡ በሕይወታቸው አያሌ ተቃርኖዎችን ለማስተናገድ ተገደዋል፡፡ ወንዶች ምክንያታዊ (Rational) ተደርገው ሲሳሉ፣ ሴቶች ግን ኢምክንያታዊ (irrational) ተደርገዋል፡፡ ወንዶቹ አዛዥና አዛዥ (dominating) ሲሆኑ፣ ሴቶች ደግሞ እጅ ሰጪ (submissive)፤ ወንድ የአደባባዩ ጌታ (public domain) ሲሆን፣ ሴቶቹ የቤት እመቤት (domestic realm) ተደርገዋል፤ የመጋቢነትና ጠብቆት (provider/protector) ሚና ለወንድ ሲሰጠው፣ ለሴት ግን በተንከባካቢነት፣ በማዕድ ቤት ስራዎችና እናትነት[6] (caretaker/mother) ሚና ይሰጣታል፤ ወንድ ኃያል/ጠንካራ ሲደረግ፣ ሴት ግን ድኩም ተደርጋ ትወከላለች፡፡ በአባዊነት የተገነባው አድሎአዊው ሥርዓት በሴት ልጅ ላይ ግፍ ሲፈጽም ኖሮ አሁንም እንደቀጠለ ነው ብለው እንስታውያኑ የሚከራከሩት ለዚሁ ነው፡፡ በሥነጽሑፍ ውጤቶች ላይም ይህ ውክልና ተጭኖባቸው ቀርበዋል፤ እንስታውያኑ በሥነጽሑፉ ውስጥ ሴቶች እንዴት እንደተሳሉ በሚገባ ይመረምራሉ፡፡

በዘልማዳዊው የጾታ ሚና ወንዴ (Masculine) ጾታዎች ያስባሉ፤ ነውጠኞች፣ ባለሙሉ የተዋረደ ስልጣን፣ ምክንያታዊ፣ ለስራ ወደ ውጪ የሚወጡ፣ ነገር አቅላይ፣ ተናጋሪ፣ እርምጃ ፈጻሚ፣ አሰላሳይ/ባለ ንቁ ህሊና፣ ጠባቂ /መከታ እና ውሳኔ ሰጪ ሆነው ተወክለዋል፡፡ በአንጻሩ ሴቷ (Feminine) ደግሞ ባለ ስስ ስሜት፣ ጨቅጫቆች፣ አቤት ባዮች፣ የጎንዮሽ ስልጣን አሸጋሻጊዎች /ደልዳዮች፣ ስሜታዊ፣ የቤት ውስጥ ስራ፣ ተብሰልሳይ/ተነዛናዥ፣ አድማጭ፣ ፍዝ ድርጊት ተቀባይ/ ደካማ እርምጃ ፈጻሚ፣ ግምታዊ/ህልመኛ/ቅዥበታዊ፣ ህጻን ተንከባካቢ/አሳዳጊ እና ውሳኔ ተቀባይ ተደርጋ በአድሎ ተወክላለች (Tyson, 2006)፡፡

ጥናቱ በዓይነታዊ (qualitative) የጥናት ሥነዘዴን ጥቅም ላይ አውሏል፡፡ ይህ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያትም የጥናቱ ጉዳይ በጽሑፋዊ ስራዎች ላይ እንደማተኮሩ ዓይነታዊ ሥነዘዴ ምርምሩን ለማካሄድ ሁነኛ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡ በዚህ ስራ የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ ለጥናቱ የመጀመሪያ ደረጃ ምንጮች

2 የእንስታዊነት ንቅናቄ የሚያተኩርባቸው ነጥቦች አሉ። የሥነ ጾታ ተጽዕኖ በጽሑፍና በንባብ ይቃኛል። አባዊውን ስርዓት በመተቸት ይጀምራል። በአብዛኛው ፖለቲካዊና አመለካከትን የመከለስ (revisionist) ገጽታ አለው። ሥነጾታ ሁሉንም ነገር ይወስናል ብለው ያምናሉ። በጾታዎች የማኅበራዊ፣ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እኩልነት ያምናል። እንስታዊ ንድፈ ሃሳብ ሴቶችን የማብቃት (empowering) ንቅናቄነው ። የወንድን የበላይነት በመተቸት እሱን ለመቀየር የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው።

3 schools of feminist criticism

4 Tyson, L. (2006). critical theory today: a user friendly guide. USA: Routledge

5 ሴቶች በአባዊ በሆነው ስሪት ተረግጠዋል። ሁሉም የምዕራብ ስልጣኔዎች በአባወራዊ ተጽዕኖ ስር የወደቀ ነው። ሴቶች እንደ "ሌላ" (other) ቶቀጥረዋል።ሥነ ጾታ በባህል የታጠረ ነው ብለው ፌሚኒስቶች ያምናሉ፤ ይህ ማለት ባህል በራሱ በአሽናፊዎቹ ለአሸናፊዎቹ አጋድሎ ይዋቀራል እሱም አባወራዊ ነው። በዚህም የተነሳ የጾታ ኢ-ፍትሃዊነት ነግሷል። ጾታ በሁሉም የሰው ልጆች የሕይወት ጥግ ላይ ይንጸባረቃል (Tyson፣ 2006)። 6 "Othering" - "ሌላነት"

6 ተፈጥሮአዊና ሰናይ ነውና የዝቅተኝነት መለኪያ ባይደረግም ቅሉ

የዘርአ ያዕቆብና ደቀ መዝሙሩ ወልደ ሕይወት የፍልስፍና መጽሐፍት ናቸው። ሁለተኛ ደረጃ ምንጮች ደግሞ የተለያዩ ቀደምት ምርምሮች፣ መጻሕፍትና ልዩ ልዩ ሰነዶች ናቸው። ከመጽሐፍቱ ላይ እንስታዊነትን የሚመለከቱ ሐሳቦች ተተንትነዋል። ከላይ በተገለፁት የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች የተገኙ መረጃዎች ከእንስታዊነት ፍልስፍና አንጻር በመሰደር የእንስታዊነትን ንድፈ ሃሳብ ርእዮቶችን ከገላጭ የትንተና ዘዴ (discriptive analysis) ጋር በማቀናጀት የሰነድ (text) ትንታኔ ቀርቧል። ጥናቱ ተተንትኖ የቀረበው ከእንስታዊነት (feminism) ንድፈሃሳብ መሠረታዊ ጭብጦች አንጻር ነው።

## እንስታዊነት በሐተታ ዘርአ ያዕቆብና ሐተታ ወልደ ሕይወት

### የዘርአያዕቆብ እንስታዊ ምልከታ

ዘርአ ያዕቆብ የአውሮፓ ዘመናዊ ፍልስፍና በተጀመረበት ዘመን የነበረ ፈላስፋ ሲሆን፣ በ17ኛው ክፍለዘመን ዘመናዊ ፍልስፍናን በኢትዮጵያ ጀምሯል። በዚህ በነጻነት የማሰላሰል ልማዱ ከአውሮፓ የዘመኑ ፈላስፋዎችና አሰላሳዮች ሊነጻጸርና ሊሻል በሚችል መልኩ ስለሴትነት ፍትህ መርምሯል። ሴት ልጅ ከወንድ ጋር በእኩልነት የመቅረብ መብት እንዳላት፣ የእንስታዊነት ንድፈሃሳብና ንቅናቄ ከመጀመሩ አስቀድሞ ግርምትን የሚፈጥሩ ምልከታዎችን ሰንዝሯል። ከዘርአ ያዕቆብ የፍልስፍና ማዳወሪያ ብልቶች ውስጥ አንደኛው ሴትነት ነው።

ሙሴና መሐመድ ሴትን በተመለከተ ያስቀመጡት ሥርዓት በዘርአ ያዕቆብ ዘንድ ተቀባይነት የለውም። ለሴት ክብር የሚመጥኑ ካለመሆናቸው የተነሳ ትምህርታቸው "ከእግዚአብሔር ሊሆን እንደማይችል[7]" ያምናል። እግዚአብሔር የፈጠረልን ብርሃናዊ ልቦና፣ እግዚአብሔር በፍጡሩ ላይ የሰራው ፍትሃዊ ሥርዓት "መልዕክተኞቹ" እንዳሉት አይሆንም ብሎ ያምናል። ሴትን ከወንድ ያሳነሰ ብቻ ሳይሆን ማኅበራዊ ህይወቷንም ለውስብስብነት ዳርጎታል። ሴት በማኅበረሰቡ ውስጥ ዝቅተኛ ቦታ፣ በተፈጥሮዋ ያነሰች፣ አናሳ ሚና ያላት ሆና እንድትታይ አድርጓታል። የዘወትር ህይወቷንም ከባድና መራራ አድርጎባታል። የሚከተለውን አስረጅ ወስደን እንመልከት፡-

የሚወለዱ ሰዎች ወንድና ሴት ቁጥራቸው ትክክል ነው። በአንድ ሰፊ ቦታ የሚኖሩ ወንድ እና ሴት ብንቆጥር ለእያንዳንዱ ወንድ አንዲት ሴት ትገኛለች እንጂ ለአንድ ወንድ ስምንት ወይም አስር ሴቶች አይገኙም ። የተፈጥሮ ሕግም አንዱ ከአንዲት ጋር እንዲጋቡ አዟል። አንድ ወንድ አስር ሴት ቢያገባ ግን ዘጠኝ ወንዶች ሴት የሌላቸው ይቀራሉ። ይኸም የፈጣሪን ሥርዓትና ሕገ ተፈጥሮን የጋብቻንም ጥቅም ያጠፋል። አንድ ወንድ ብዙ ሴቶች ሊያገባ ይገባዋል ብሎ በእግዚአብሔር ስም ያስተማረ መሐመድ ግን ትክክል ነው አልልም[8] ። ከላይ የተቀመጠው ሐተታ ዘርአ ያዕቆብ ስለመሐመድ የሰነዘረው ነው ። ተፈጥሮአዊ የሆነውን መንገድ ልቦናችን እንደሚመራን፣ አንዲት ሴት ለአንድ ወንድ የተፈቀደች፣ አንድ ወንድም ለአንዲት ሴት የተፈቀደ ነው ። "ጥቂት ስለጋብቻ መረመርኩ[9]" ይላል፤ በምርመራውም የተጠቀሰው የመሐመድ ስራት ለሴቷ ፍርደ ገምድል ሆኖ እንደተሰራ ያምናል ። አንድ ሰው ስምንት ወይም አስር ሴቶችን የሚያገባ ከሆነ፣ ቀሪዎቹ ወንዶች ለሚስት የምትሆናቸውን ሴት ያጣሉ። ሴቷ ደግሞ በጋብቻ ወግ ከወንዱ ልታገኝ የሚገባትን ማዕረግ ማግኘት አትችልም፤ አንድ ሰባተኛ ድርሻ ብቻ ይኖራታል፤ የሚገባትን የራሷ የሆነ አንድ አጋር ማግኘት አልቻለችም፤ ሴቷ የሚስትነት ወግን ብቻ ሳይሆን ጾታዊ ተራክቦን በፍላጎቷና ልታገኝ በሚገባት ጊዜ መጠን ማግኘት ላትችል ነው።

እንደዘርአ ያዕቆብ ገለጻ "ፈጣሪ ያቆመው ስርዓት ሁሉ ቅን ነው"10። ስለዚህ ከተፈጥሮ ሥርዓት ጋር የማይስማማ ወይም ሥርዓቱ ሁሉ ቅንና ፍጹማዊ ከሆነ ፈጣሪ ባህርይ ጋር የማይጣጣም ሁነት ሊኖር አይችልምና "ሰዎቹ" ህጹጽ በሆነ የሰው ልጅ አዕምሮ የሰሩት ስህተት ነው ብሎ ያምናል። ዘርአ ያዕቆብ ሴትን አስመልክቶ በሙሴ የነበረውን ሥርዓት እንዴት እንደተቸው ቀጥሎ በተቀመጠው ቅንጭብ ጥቅስ ማሳያነት እንመልከት።

> ፈጣሪ በመልካም ጥበቡ ከሴት ልጅ ማህፀን በየወሩ ደም እንዲፈስ አድርጓል። ይህ የደም መውረድ ለሴት ሕይወት እና ልጆች ለመውለድ ያስፈልጋል ። ይህ ደም የማይወርዳት ሴት መካን ነች ። መውለድ አትችልም ። ምክንያቱም ፍጥረቷ ተበላሽቷልና ነው ። ሙሴና ክርስቲያኖች ግን ይህን የፈጣሪ ጥበብ እርኩስ አደረጉ ። እንደገና ሙሴ እንዲህ ያለችውን ሴት የተገናኛትን ያረክሳል ። ይህም የሙሴ ሕግ የሴትን ኑሮ በሙሉ እና ጋብቻዋን ከባድ አድርጎታል ። የመራባትንም ሕግ አጥፍቷል። ልጆችን ከማሳደግ ከልክሎ ፍቅርንም ያፈርሳል ። ስለዚህም ይህ የሙሴ ሕግ ሴትን ከፈጠረ ሊሆን አይችልም[11]።

እንደመሐመድ ሁሉ ዘርአ ያዕቆብም የሙሴን ሕግ ይተቻል ። ሙሴ እግዚአብሔር የሰራውና ተፈጥሯዊ በሆነ መልኩ ከሴት ልጅ የሚወጣውን "ደም" (የወር አበባ) ስለምን የእርኩሰት መገለጫ ያደርጋል ብሎ ይሞግተዋል። እንደዘርአ ያዕቆብ የወር አበባ የትውልድ መቀጠያ መንገድ ነው ። ስለሆነም ሴቷ ልትገለልበት፣ ከማኅበረሰቡ እንድትነጠል የምትደረግበት ጉዳይ ሊሆን አይገባም። ይሄ እሳቤ የሴትን ኑሮ ውስብስብ ጋብቻዋንም ከባድ እንዳደረገው ይከራከራል። ልጆችን ለማሳደግ አስቸጋሪ እንዳደረገ፣ በትዳር ውስጥ ያለውን ፍቅርም እንደሚያደበዝዝ ዘርአ

---

7 ዘርአ ያዕቆብ (በዳንኤል ወርቁ ትርጉም)

8 ዳንኤል ወርቁ (አሰናጅ)። (2007)። ሐተታ ዘርዓ ያቆብ እና ሐተታ ወልደ ሕይወት። አ/አበባ፤ (ዓመተምህረት የሌለው)።

9 ዘርአ ያዕቆብ (በዳንኤል ወርቁ ትርጉም)

10 ዘርአ ያዕቆብ (በዳንኤል ወርቁ ትርጉም)

11 ዳንኤል ወርቁ (አሰናጅ)። (2007)።ሐተታ ዘርዓያቆብ እና ሐተታ ወልደ ሕይወት።አ/አበባ፤ (ዓመተ ምህረት የሌለው)።

ያዕቆብ ይሟገታል። በዚህ ተፈጥሯዊ ምክንያት የወር አበባ ያየች ሴት ጋር ተራክቦ የሚፈጽምን ሰው ሙሴ ርኩስ ማድረጉ ተገቢ እንዳልሆነ ይሄሳል። ለዚህም ነው ይህ ሕግ "ሴትን ከፈጠረ ሊሆን አይችልም" ብሎ ፈላስፋው የሚከራከረው ። ነገር ግን ዘርአ ያዕቆብ ከኦሪት ጋር ደርቦ ክርስትናን በነገረ ጾታ መወንጀሉ የሚዋጥ አይደለም[12] ።

አጼ ሱስንዮስ ሞቶ ልጁ አጼ ፋሲለደስ ከነገሠ በኋላ ሰላም ሲመለስ ከተደበቀበት ዋሻ ወጣ ። በመንገዱም በምድረ እንፍራንዝ ከጌታ ሃብቱ ዘንድ ተገናኘ ። መዝሙረ ዳዊትን እየጻፈ፤ የሃብቱን ልጆችንም በማስተማር ዋጋውን ያገኝ ነበር ። በሃብቱ ቤት ሒሩት የተባለች አገልጋይ ነበረች ። እሷንም ያገባት ዘንድ ወርቂ ወደደ ። ልጂቷን እንዲህ ይገልጻታል፤ "ምግባረ መልካምና ልባም፣ ትዕግስተኛ እንጂ ደምግባታም አይደለችም"14 ። ዘርአ ያዕቆብ የልጂቷን ባለመልካም ምግባርነት፣ ልባምነትና ትዕግስተኛነት ተገንዝቧል፤ ይህንንም አድንቋል ። መልኳ ግን አይነግቡ አልነበረም፤ ይህ መሆኑም ግድ አልሰጠውም ። ከዚህ የምንገነዘበው ውስጣዊ ውበት (ምግባረ መልካምነቷ፣ ልባምነቷና ትዕግስተኛነቷ) እንጂ፣ ደም ግባት (መልክ) ለዘርአያዕቆብ ቦታ አልነበረውም። በዚህም ምክንያት ዘርአ ያዕቆብ ሴትን ለመጠቀሚያነት /ለግል እርካታ (Comodify) አድርጎ አላሰባትም ። ቆንጆ እንድትሆን፣ በቤት ውስጥ ስራ እንድትገደብ፣ ልጆች እንድትወልድለት ብቻ አልፈለጋትም፤ እሷነቷን፣ ያላትን ማንነት ተመልክቶ ወዷታል፣ ሚስት ትሆነው ዘንድም ሽቷታል ።

"ይህቺ ልጅ ሚስት እንድትሆነኝ ስጠኝ" አልኩት ።

"እሺ ከእንግዲህ ባሪያህ እንጂ ባሪያዬ አይደለችም።" ሚስቴ ካልሆነች በስተቀር ባሪያዬ አይደለችም። ወንድና ሴት በጋብቻ በአንድ ስጋና በአንድ ንብረት ትክክል ናቸው እና ጌታና ባሪያ ልንላቸው አይገባም።" አልኩት። ጌታዬ ሃብቱ

"አንተስ የእግዚአብሔር ሰው ነህና እንደፈቃድህ አድርግ" አለኝ። ያችንም ሴት ጠራትና እኔም

"ሚስቴ ልትሆኚ ትወጃለሽን" አልኳት።

"ጌታዬ እንደፈቀደ" አለችኝ። ጌታዬ ሃብቱም

"እኔስ እፈቅዳለሁ" አላት። እርሷም

"ከአንተ እሚበልጥ የት አገኛለሁ መልካም" አለችኝ[13]።

በዚህ ንግግር (dialogue) ውስጥ ዘርአ ያዕቆብ ከሚያከብረው፣ ስምና ባለ ጸግነት ካለው "ጌታዬ" እያለ ከሚጠራው ሃብቱ ጋር ሳይቀር ስለሴት መብት ለመከራከር አላመነታም፤ አልፈራምም ። እንደዘመኑ ልማድ "ባሪያህ" ትሁንህ ሲባል፣ አይ "ሚስቴ ካልሆነች በስተቀር ባሪያዬ አይደለችም" ብሎ አሻፈረኝ ብሏል። መጀመሪያውንም ጥያቄ ሲያቀርብ ሚስቱ እንድትሆነው ነው። ከዚያም "ጌታዋ" "ባሪያህ ትሁንህ" ሲለው፣ የሰውን ልማዳዊ ይትበሃልም፣ አመለካከቱንም ከማረም ጋር አብሮ ተቃውሞታል። ይህ አነጋገሩ ለጌታው ለሃብቱ ሳይቀር "አንተስ የእግዚአብሔር ሰው ነህና እንደፈቃድህ አድርግ" ብሎ እስከመደመም አድርሶታል። በሃብቱ[14] አረዳድና የይሁንታ ስምምነት ሒሩት እና መሰሎቿ "ባሪያዎች"[15] እንጂ ከሰው እኩል ስም አልነበራቸውምና ከሰው እኩል ዋጋ ሰጥቶ አክብሮ "ሚስቴ" ማለቱ አንድም የተናቀችውን "ባሪያ" አክብሮ ለጋብቻ መጠየቁ ሃብቱን አስደንቆታል ። ይህ የወርቂ አስተሳሰብ ሃብቱን እጅግ ስላስደነቀው የእግዚአብሔር ሰው (የተቀደሰ) እንደሆነ እንዲያስብ አድርጎታል ። "ባሪያ"ን አንድም ሴትን አክብሮ ሚስቴ ማለቱ አስደንቆታል፤ የማይደፈር እሳቤ ነበርና።

ወርቂ "ወንድና ሴት በጋብቻ በአንድ ስጋና በአንድ ንብረት ትክክል ናቸውና ጌታና ባሪያ ልንላቸው አይገባም" ብሎ ነበር የተከራከረው። ይህ አመለካከት አስደናቂ እንደሆነ በተለይ የዘመኑን አውድ ተመልክተን እንገነዘባለን፡ ፡ ሒሩትንም በክብር "ሚስቴ ልትሆኚ ትወጃለሽን" ብሎ ሲጠይቃት፣ አዎን ወይም እምቢ አላለችም፤ "ጌታዬ እንደፈቀደ" ነበር ያለችው። ይህም በዘመኑ ማኅበረሰባዊ አውድ ሴቶቹ ሳይቀሩ ተገዥነታቸውን አምነው ተቀብለዋል[16] ።

ከዚህ አውድ መገንዘብ የምንችለው ሴቶች ለባርነት የሚዳረጉ ከሆነ የሁለት እጅ ጉዳት ሰለባ እንደሚሆኑ ነው ።

---

12 ከክርስቲያኖች ወንጌል ላይ (ሙሴና መሐመድ ላይ እንዳደረገው) ማስረጃ ማቅረብ አልቻለም። ምናልባትም ለመሐመድ ቁራን ላይ እንዳገኘውና ለሙሴም መጽሐፍ ቅዱስ (የብሉይ ክፍል) ላይ እንዳገኘው አመለካከቱን የሚደግፍ ማስረጃ ወንጌል ላይ ማግኘት ባለመቻሉ ይሆናል፡ ፡ ወንጌል በተሻለ ለሴቶች እኩልነት ዋጋ መስጠቷ እሙን ስለሆነ። መሐመድን ከአንድ በላይ ማግባትን አስመልክቶ ለሰነዘረው፣ ሙሴ ላይም ላነሳው እይታ የኃይማቱ መሪዎች (አማኞች) ቅቡል የሚያደርጉበት ምክንያት (አንድምታ ትርጉም) ይኖራቸዋል። እዚህ ላይ የተንጸባረቀው ግን የዘርአ ያዕቆብ ሃሳብ እንደወረደ ነው። በሌላ በኩል ፈላስፋው ስለእስልምና የሚያውቀው ምናልባት ውስን ሳይሆን አይቀርም። ፍልስፍናውን ያካሄደበት አካባቢ ለእስልምና ሩቅ መሆን ልሂቃኑን በቀላሉ አግኝቶ የሚያወያይበት እድሉን አናሳ ያደርግበታል። ስለሆነም መሐመድ "ብዙ" ማግባትን ይፈቅዳል ከሚለው የጎነ መረጃ ላይ ተመስርቶ የተናገረው ይሆናል። ስለኦሪትና ክርስትና ለማወቅ ግን አካባቢው በሚገባ አመቺ ነው፡ ፡ ሃገሩ እንፍራንዝ/ጎንደር ነው፤ ኦሪትን ለመመርመር ፈላሻ እና/ወይም ቅማንት፣ ክርስቲያኖችን መጠየቅ ወይም ያደገበት ትምህርት ስለሆነ በራሱ ማወቅ ይችላል። ስለክርስናም ቢሆን ኦርቶዶክስ ክርስቲያኑ እንዳለ ሆኖ ካቶሊኮችም በሱስንዮስ ዘመን በአካባቢው በስፋት ተንሰራፍተው ስለነበር ከልሂቃኑ (ከነአልፎንሱ. ከነፓኤዝ) ጠይቆ መረዳት የሚያስችል እድል አለው። 14 ዘርአ ያዕቆብ (በዳንኤል ወርቁ ትርጉም)

13 ዳንኤል ወርቁ (አሰናጅ)። (2007)።ሐተታ ዘርዓያቆብ እና ሐተታ ወልደ ሕይወት።አ/አበባ፤ (ዓመተ ምህረት የሌለው)።

14 የዚያን ዘመን ማኅበረሰብ ሊወክል ይችላል

15 አገልጋይ/ባሪያ በመሆናቸው ለሁለቱም ጾታዎች እኩል የደረሰባቸው መጥፎ እጣ ፋንታ ወይም በማኅበረሰቡ የተሰጣቸው የወል ቦታ ነው። ሴቶች ሲሆኑ ደግሞ "ባሪያ"ነታቸው እንዳለ ሆኖ ሴትነታቸውም የዝቅተኛነት መገለጫቸው ሆኖ በአባዊው ልማድ ተሰርቷል። ስለሆነም አንድ ወንድ አንዲትን ሴት ለጋብቻ ሲፈልግ እኩል አጋሩ እንድትሆን ሳይሆን አገልጋዩ ወይም "ባሪያው" እንድትሆንም ጭምር ነበር። ሴትን እንደንብረት መቁጠር አሁንም ቢሆን ያልቀረ ቀድሞ በአባዊው አሰራር የተዘረጋ ልማድ ነው። ዘርአ ያዕቆብ ይህንን ልማድ በመጻረር ያሳየው ተጋድሎ በተለይ ከዘመኑ ርቀት አንጻር ሲታይ እጅግ የሚያስደንቅ ነው።

16 ምንም እንኳ ሒሩት ሴትነቷ ብቻ ባይሆንም ከመነሻው በባርነት ስር መሆኗ የ"ጌታዋን" ፈቃድ እንድትጠይቅ ያስገድዳታል፡ ፡

አንድም በሴትነታቸው፣ አንድም በባርነታቸው ። ዘርአ ያዕቆብ ባሪያ ተብላ የተፈረደባትን ሴት ሳይንቅ እንደሰው ቆጥሮ ሚስት ሁኚኝ ብሏታል። እዚህ ላይ ሁለት ነገሮችን እናንሳ። አንደኛው ባሪያ የተናቀ ነበርና ባርነቷን ሳይንቅ እኩል ሰው መሆኗን አስቦ ለጋብቻ መጠየቁ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ባሪያ ባይሆኑ እንኳ ሴቶች በሴትነታቸው ዝቅተኛ ስፍራ ስለሚሰጣቸው በክብር የጋብቻ ጥያቄ ለማቅረብ ዘልማዳዊው የጾታ ሚና አለመፍቀዱ /ከሚስት በላይ/በተጨማሪ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ሚስት ተደርገውም ለጾታዊ ፍላጎት የሚፈጸም ጋብቻም አለ)። በመሆኑም የጋብቻ አጠያየቁ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ፣ ለሴት ክብር የሚሰጥና የሚስትነት ማዕረግ የጠበቀ አልነበረም። ዘርአ ያዕቆብ ግን ይህንን ሁሉ ዘልማዳዊ ፍርደ ገምድል ወግ በመጣስ እንስታዊ አመለካከቱን ያሳየ ፍትሃዊ ጥያቄ አቅርቧል። እዚህ ላይ ዘርአ ያዕቆብ ሰብአዊ ክብሯን ጠብቆ፣ የትዳር ምርጫዋን አክብሮ ፈቃደኝነቷንም ጠይቋል ።

ይህችም ሒሩት ሚስቴ ሆነችና በጣም ወደደችኝ ። በጌታዬ ሃብቱ ቤት የተናቀች ነበረችና፤ ቤተሰቦቿም ዘወትር ያሳዝኗት ስለነበሩ ዛሬ በጣም ተደሰተች። እኔም፣ ስለወደደችኝ በተቻለኝ ሁሉ እንዳስደስታት በልቤ ወሰንኩ። …. ከሚስቴ ጋር በፍቅር ነበርኩ። እኔ እየጻፍኩ የጌታዬን ሃብቱን ልጆች ሳስተምር እርሷም ቀንና ሌሊት ትፈትል ነበር[17]።

እዚህ ላይ ሴቷን ከእርሱ ጋር እኩል እያደረገ የሚገልጽበት መንገድ አስደናቂ ነው። ስለወደደችው እንዲሁ ተቀብሎ አልተዋትም፤ ይልቁንም እሱ መልሶ አብልጦ እንዴት እንደሚወዳት ይጨነቅ ነበር ። መዋደድ ከሁለቱም ወገን መምጣት እንዳለበት ያምናል ። በንብረት ክፍፍልም እኩል ነበሩ ። የሚያገኙትን ሁሉ እኩል እንዳገኙና እኩል የንብረት ተካፋይነት መብት እንዳላቸው ይናገራል፤ በስራ ክፍፍልም እንደዚሁ፤ እርሱ በመጻፍና በማስተማር ገቢ ያገኛል፤ እሷ በበኩሏ ተግታ በመፍተል ገቢ ታስገኛለች ።

ፈላስፋው ሴቶችን በገለጸበት አንቀጹ ሁሉ ሴቶች ባለመልካም ምግባር፣ ሰው ወዳድ፣ ትሁት፣ የከበሩ፣ ደግ እንደሆኑ አድርጎ ነው ። ለሴትነት ያለው ምልከታ አዎንታዊና በቀናነት የተሞላ መሆኑን ያሳያል ። ዘርአ ያዕቆብ ፈጣሪ ተፈጥሮን ውብ አድርጎ ማነጹን ደጋግሞ ይናገራል ። ሴትም የፈጣሪ ውብ ስራ ናት፡ ፡ ለተፈጥሮ የሚኖረን የተዛባ ምልከታ ሴትን እንድናገላት ይገፋል። እንደፈላስፋው ምልከታ ሴት በእግዚአብሔር ውብ እጆች በጥበብ ከተሰራች ዘንድ እኛም ልናከብራት ይገባል፤ አሊያም ፈጣሪዋን እንደመገዳደር ነው ።

## የወልደ ሕይወት (ምትኩ) እንስታዊ ምልከታ

ወልደ ሕይወት እንደመምህሩ ሁሉ ሴቶችን በተመለከተ እንስታዊ ምልከታ አንጸባርቋል። የወልደ ሕይወትን ምልከታ ለየት የሚያደርገው ሴቶች አልጋ ላይ በሚፈጸም ግብር ሳይቀር ከወንዶች ጋር በእኩል ስለሚኖራቸው የእርካታ ድርሻ ድረስ ዘልቆ ይመረምራል ። እንደመምህሩ ሙሉ ለሙሉ የሴት ደጋፊ ነው ባንለውም ስለሴቶች መብት በአሁኑ ዘመን ሊነሱ የሚከብዱ ጉዳዮችን ሳይቀር ደፍሮ አንስቷል ። ፌሚኒስቶች ሊቀበሉት ከማይፈልጉት አንዳንድ አስተያየቶቹ ውጭ ምትኩእንስታዊ እይታን በሚገባ አንጻባርቋል ።

በእኛ ማኅበረሰብ ውስጥም ሆነ በምዕራቡ ዓለም ሴቶችን የምናይበት መንገድ የተንሸዋረረ መሆኑ ግልጽ ነው። ሩሶ የተባለው ምዕራባዊ ፈላስፋ "ሚስት ባሏን መንከባከብና ማስደሰት ዋነኛ ተግባሯ ነው"[18]ይላል ። ከላይ እንደተጠቀሰው፣ ሚስቱ ዘርአ ያዕቆብን ስለወደደች መልሶ "በተቻለው መጠን" ሊያስደስታት ማሰቡን አይተናል። ስለዚህ ማፍቀርና መንከባከብ በሁለቱም አቅጣጫ የሚመጣ እንጂ የሴቷ ብቻ አይደለም። ወልደ ሕይወትም በተመሳሳይ ፍቅር በመስጠት፣ እርስ በርስ በመዋደድም ሆነ በስጋዊ ግንኙነት ወቅት በእኩል መጠን በጋራ የሚፈጸም መሆኑን ያስረዳል። ወልደ ሕይወት "የሩካቤን ጣዕም ከሚስትህ ጋር ተካፈለው እንጂ ለብቻህ አትሻው[19] " ይለናል። በትዳር ውስጥ የሚፈጸም ሩካቤ ሳይቀር በእኩልነት መጠን የሚፈጸም ጉዳይ እንጂ ወንዱ ብቻውን ለግሉ እርካታ የሚፈጽመው፣ ብቻውን የሚደሰትበት አለመሆኑን በግልጽ ያስተምራል። ሚስትህ የሩካቤን የመጨረሻ ደስታ እስክታገኝ ድረስ ጠብቃት፣ ደስታውን አብረኻት ተካፈለው እንጂ ለብቻህ አትሻተው ብሎ ወንድን ያስገነዝባል።

"…ሴት ከሌለችህ አግባ፣ ባል ከሌለሽም አግቢ[20] " ። እዚህ ላይ ልብ የምንለው ለወንዱ ብቻ አይደለም አግባ ያለው ። አግባ! አግቢ! ሲል፣ አንደኛውን ወገን (ጾታ) ብቻ ለይቶ ሳይሆን ሁለቱንም በእኩልነት አውድ ነው። አውስቦ የተገባና በፈጣሪ የተሰጠ እንደመሆኑ ፍትወት መፈጸም (ሁለቱም ፈላስፎች ሩካቤ በጋብቻ ውስጥ ብቻ እንዲሆን ይመክራሉ) ተገቢ ነው። እሱን ለማድረግ ወንዱ ብቻ መብቱ ተደርጎ፣ ሴት እንደስሜት ማርኪያ ሆና መታሰቧ ተገቢ አለመሆኑን ሲያጠይቅ፣ እሱን "አግባ!"፣ እሷንም "አግቢ!" ነው ያለው ። "…ከአንዷ ወደ ሁለተኛዋ አይሂድ። ሴትም የማይጠቅም ዝሙት ነውና ከወንድ ላይ ወንድ አትውደድ[21] "። ማመንዘርንም ሲከለክል በእኩልነት ነው። እንደዘልማዳዊው ማኅበረሰብ ወንድ ከአንድ በላይ ይይዛል፤ እቁባት፣ ውሽማ፣ ቅምጥ የሚባሉ ዓይነቶችን ክፉ ልማዶች ልብ ይሏል ። በዚህ ልማድ ወንዱ በብዛት በማኅበረሰቡ አይተችም፤ ሴት አድርጋው ብትገኝ ግን "ትወገር" ባዩ ብዙ ነው ። ወልደ ሕይወት ግን ሁለቱም በእኩል መጠን ከዝሙት እንዲርቁ አሳሰበ እንጂ ልዩነት አልፈጠረም ። "እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ ። ከእንግዲህ ሌላ ወንድና ሌላ

---

17 ዳንኤል ወርቁ (አሰናጅ)። (2007)።ሐተታ ዘርዓያቆብ እና ሐተታ ወልደ ሕይወት።አ/አበባ፤ (ዓመተ ምህረት የሌለው)።

18 ብሩህ ዓለምነው። (2009፡122)። የኢትዮጵያ ፍልስፍና። አዲስ አበባ፤ (አሳታሚ ያልተገለጸ)።

19 ሐተታ ወልደ ሕይወት (በዳንኤል ትርጉም፣ 2007፡ 66)

20 ሐተታ ወልደ ሕይወት (በዳንኤል ትርጉም፣ 2007፡ 66

21 ሐተታ ወልደ ሕይወት (በዳንኤል ትርጉም፣ 2007፡ 66)

ሴት አትውደዱ[22]”። ይሄ ድንቅ ሐሳብ ነው፤ ጾታን በገለጸበት አንቀጽ ሁሉ ላይና ታች አድርጎ አልገለጸም።

> “ትዕቢት እንዳይዛት መልከ መልካምና ከበርቴ የሆነች ሴት አታግባ። የአውስቦ ፍቅር ከትዕቢት ጋር አይስማማምና፡ ፡ ሴትም እንዳይንቃትና ወደሌላ እንዳይሄድ ትዕቢተኛና ኃይለኛ ወንድ አታግባ።... ወንድና ሴት ከተጋባችሁ በኋላ አንድ እንጂ ሁለት ሥጋ አይደላችሁምና እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ። ከእንግዲህ ሌላ ወንድና ሌላ ሴት አትውደዱ፤ ነገር ግን አንዱ ለሁለተኛው በፍጹም ፍቅር እና በተቻላችሁ ሁሉ ደስ አሰኙ፡፡”[23]

መልከ መልካም እና ከበርቴ የሆነች ሴት ትዕቢተኛ ናት ዓይነት ትርጓሜ ያለው ሐሳብ ነው ። እዚህ ላይ ሴትን የተቸ ቢመስልም ቅሉ፣ በአንጻሩ ወንዱንም ተችቷል ። ትዕቢተኛና ኃይለኛ ወንድ ሲንቅ፣ ወደሌላም ሊያይ ስለሚችል የምታገባው አይሁን ይላል፡ ፡ በሁለቱም ወገን ድክመት ያለውን ነቅሷል እንጂ ሴትን ብቻ ለይቶ ለግምገማ አላቀረበም ። መልከ መልካምነት፣ ባለጸግነት፣ ትዕቢተኝነትና ኃይለኝነት አንዱ ሌላኛውን በፍቅርና ትህትና እንዳይቀበለው፣ አልፎም የተሻለ ፍለጋ እንዲያማትሩ ስለሚጋብዝ ከሴቷም ከወንዱም በኩል ደግ ያልሆኑ ገጸ ባህርያት ተደርገው ተገልጸዋል። በእኛ ማኅበረሰብ በተለይ ስለወሲብ ማውራት ጸያፍ ተደርጎ አሁንም ድረስ ይወሰዳል ። ወልደ ሕይወት ግን ርዕሰ ጉዳዩን በግልጽ አንስቶታል። አሁንም ድረስ ወንዱ ለግል ስሜቱ እርካታ ይጨነቃል እንጂ ሴቷን አያቋጥርም፤ ይህንን ይቃወምና ወንድ ለግሉ ብቻ ሳይሆን፣ ለሴቷም የስሜት መርካት ድርሻ እንዳለው አበክሮ ያስገነዝባል።

በሌላ መልኩ ወልደ ሕይወት ሴትን ጨቅጫቃ፣ ደካማ፣ አእምሮዋም ምሉዕነት የሚጎድለው አድርጎ ከመምህሩ በራቀ ሁኔታ ወክሏታል ። ከእንስታዊነት መፈክር አንጻር ሊተች የሚችል አቀራረብ ነው። ነገር ግን አንዷን አግብቶ ፈትቶ ሌላዋን ለማግባት የሚከጅል ሰው የተሻለ ነገር እንደማይገጥመው፣ ይልቁንም ሰላም እንደማይሆን በምሳሌ እያስደገፈ ግለሰብ ሴቶችን ጠቅሶ ለባላቸው የከፉበትን ማሳያ ሲጠቅስ እንጂ በጠቅላላው ሴት ልጅን ምሉዕነት የጎደላት አድርጎ አልሳላትም። በመሆኑም ሴታዊ ምልከታው ላይ ጥላሸት የመቀባቱ እውነታ ውኃ የሚያነሳ አይደለም።

## *መደምደሚያ*

ኢትዮጵያ ውስጥ ስለሴት መብት ከተሟገቱ ግለሰቦች፣ ቡድኖችና ድርጅቶች በላይ፣ ዘርአ ያዕቆብና ወልደ ሕይወት ተሟግተዋል ብሎ ያለማጋነን መናገር ይቻላል ። የፈላስፋዎችን የነገረ ጾታ እይታ ድንቅ የሚያደርገው ደግሞ እሳቤውን ያፈለቁት ከ350 ዓመታት በፊት በ17ኛው ክፍለዘመን መሆኑ ነው ። ለኢትዮጵያ የነገረ ጾታ አረዳድና ለሴቶች መብት መከበር ያደረጉት አስተዋጽኦ ተመን የለሽ ነው። በዘመኑ የነበሩ ምዕራባውያን ፈላስፎች ሳይቀር ስለሴት ልጅ አሉታዊ አመለካከትን ባንጸባረቁበት ወቅት ኢትዮጵያውያኑ ፈላስፎች ስለሴት እኩልነት ተከራክረዋል ። ከቅድመ ክርስትና ፈላስፎች አርስቶትል ጸላኤ ሴት (Misogyny) ተጽዕኖ የታየበት ሴታዊ ግንዛቤ ነበረው። እነ ሩሶን የመሰሉ የ18ኛው ክፍለዘመን የምዕራብ አሰላሳዮችም ቢሆን ሴትን (በተለይ ቁንጅናዋን) ለወንድ ጾታዊ ፍላጎት ማርኪያነት እንደምትውል አድርገው በመሳል፣ ማኅበራዊ ተሳትፎዋ የተገደበና አናሳ እንደሆነ አድርገው በማቅረብ ይተቻሉ። ነገር ግን የ17ኛው ክፍለዘመን ኢትዮጵያዊው ፈላስፋ ዘርአ ያዕቆብ እና ደቀ መዝሙሩ ወልደ ሕይወት ሴትን ልጅ እንደወንድ እኩል እውቅና የቸሩና አልፎም መብቶቿ ሁሉ ከወንድ እኩል መሆናቸውን አስረግጠው ተከራክረዋል። በጾታዊ ግንኙነት ለወንዱ ስሜት ማርኪያነት ሳትሆን፣ እሷም እኩል እንደወንዱ የመርካት መብት የተሰጣት መሆኑን የዚህ ዘመን አቀንቃኞች እንኳ ደፍረው ለመናገር በሚከብዳቸው መልኩ ተሟግተዋል። በጋብቻ ንብረት በማፍራት ጊዜ፣ ሴቷ ከወንዱ እኩል ባለቤትነት እንዳላት፣ በጋብቻ ወቅት እንደአገልጋይ ሳይሆን እንደሚስት እኩል መብትና ድምጽ እንዳላት ተናግረዋል። የኃይማኖት መልዕክተኞች በሴቷ ላይ አግባብ ያልሆነ ሕግጋትን በማውጣት ሴት እንድትገለል ሆኗል ብለው ኃይማኖቶችን ይተቻሉ። ዘርአ ያዕቆብ ትዳር ባሰበ ጊዜ የሴቷን ምርጫ አክብሮ ፈቃደኝነቷንም ጠይቋል። የሴትን መብት በተግባር ራሱ ቀድሞ አሳይቶ እንዲከበር የሚጠይቅ ነው። ፍቅርን በእኩልነት መስፈርት ተቀብሎ በመስጠትም ያምናል፤ ስለወደደችው እንዲሁ ተቀብሎ አልተዋትም፤ ይልቁንም እሱ መልሶ አብልጦ እንዴት እንደሚወዳት ይጨነቅ ነበር። በንብረት ክፍፍልም እኩል ነበሩ። የሚያገኙትን ሁሉ እኩል እንዳገኙና እኩል የንብረት ተካፋይነት መብት እንዳላቸው ይናገራል። በስራ ክፍፍልም እንደዚሁ። እርሱ በመጻፍና በማስተማር ገቢ ያገኛል፤ እሷ በበኩሏ ተግታ በመፍተል ገቢ ታስገኛለች። ከሴት ልጅ ጋር አብሮ በፍቅር በመኖር በእኩልነት ያምናል ። የአውሮፓ እንስታዊ ንቅናቄ ባብዛኛው የተመራው በሴት አነቃናቂዎች ነው። የ17ኛው ክፍለዘመን የኢትዮጵያ ፍልስፍናን የመሩት እነዚህ አሰላሳዮች ግን ወንድ ሆነው ሳለ ነው ስለሴት ልጅ የማኅበራዊ ፍትህ ጥያቄዎች አጥብቀው የተሟገቱት። ስለሴት ልጅ እኩልነት፣ ማኅበራዊ ፍትህ፣ ሰብአዊ ክብር፣ ንብረትን በእኩልነት የማፍራትና የባለቤትነት መብት፣ በጋብቻና ትዳር ወቅት ከባል ጋር እኩል የመወሰን መብት፣ ሴት እንዳላት ፈላስፋዊያኑ ይከራከራሉ ።

እንደአውሮፓውያኑ ሁሉ ዘርአ ያዕቆብ እና ወልደ ሕይወት የኖሩባት ኢትዮጵያ ነባራዊ አውድ በአባዊ (patriarchal) ሥርዓት የሚዘወር ነበር ። በዚህም የተነሳ በማኅበረሰቡ ውስጥ ሴቷ የተሰጣት ሚና ዝቅተኛና “የሌላነት” ነበር። ፈላስፋዎቹ ይህን ነባራዊ እውነት ነው ለማስቀረት የታተሩት። እነዚህ ሐሳቦች ውጫዊ ቅጂ የሌላቸው፣ በጥልቅ ከመመርመርና

22 ሐተታ ወልደ ሕይወት (በዳንኤል ትርጉም፣ 2007፡ 66)

23 ሐተታ ወልደ ሕይወት (በዳንኤል ትርጉም፣ 2007፡ 66)

ከማሰላሰል የመጡ ናቸው ። እንደዚህ መሰል ጠንካራ የሥነ ጾታ ጥያቄዎችን አውሮፓውያንም መሰንዘር የጀመሩት በኋላ ላይ ነው፤ በተለይ በ19ኛው ክፍለዘመን ነው በርትተው መሟገት የጀመሩት። ኢትዮጵያውያኑ ቀድመው ስለሴት መብት ተመራምረዋል፤ በጽሑፍም፣ በንግግርም አቋማቸውን አብራርተዋል። ዘርአ ያዕቆብ ሥነ ጾታን በተመለከተ ከኦሪት ጋር ደርቦ ክርስትናን መወንጀሉ የሚዋጥ አይደለም፤ ወንጌል በተሻለ ለሴቶች እኩልነት ቦታ መስጠቷ በግልጽ ስለሚታይ ። እንደዘርአ ያዕቆብ፣ ፈጣሪ ተፈጥሮን ውብ አድርጎ አንጿል። ሴትም የፈጣሪ ውብ ስራ እንደመሆኗ ልናከብራት ይገባል፤ አሊያም ፈጣሪዋን እንደመገዳደር እንደሆነ ይናገራል። ምትኩ ከመምህሩ አንጻር መሳ ለመሳ ያልሄደበትና በፌሚኒስቶች ዘንድ ሊያስተቸው የሚችል እይታ ቢያንጻባርቅም፣ ሁለቱ ፈላስፋዎች አስደማሚ እይታን ስለሴት ልጅ አውስተውን አልፈዋል።

የማኅበረሰቡን አመለካከት፣ በተለይ በሴቶች አረዳድ በኩል ሊገነባ የሚችለው ይህ የፈላስፋዎቹ ምክረ ሐሳብ ቀጥሏል ወይ? ብሎ መጠየቅ ያሻል ። በኢትዮጵያ ታሪክ ለሴት ልጅ ከፍ ያለ ቦታ የተሰጠባቸውን በርካታ አውዶች መጥቀስ ይቻላል፤ በተለይ በፖለቲካው መድረክ ። በእንስታውያን መነጽር ሲታይ ግን የፈላስፎቹ ምክረ ሐሳብ አሁን ላይ ቀጥሎ ግቡን መቷል ለማለት አንደፍርም ። ምንም እንኳ የሴት መገፋት ዓለማቀፋዊ ገጽታ ቢኖረውም ከላይ የተዘረዘሩት ማሳያዎች ሀገር በቀል እውቀታችንና የሴት አገነዛዘባችን ለሴትነት፣ በአንጻሩም ቢሆን መጠነኛ ቦታ በታሪካችን ተሰጥቶት እንደነበር እናስባለን። በአሁኑ የሀገራችን ማኅበረሰባዊ ተዋጽኦን ስንመለከት፣ ሴትነት የሚገባውን ቦታ አላገኘም፤ ከእንስታዊነት ንድፈሃሳብ አንጻርም ሲቃኝ እውነታው ይኸው ነው። የፈላስፋዎቹ ከ350 ዘመን በፊት የተንጸባረቀው ፍትሃዊ ሴታዊ ምልከታ ግን የላቀ ነበር ።

## References

Getatchew Haile. (2014). *Hatata Zara-Yaqob Bemebal Yemitaweqew*

*YeWorqe Tarik*. Collegeville, MN.

Daniel Worku. (2015). *Hatata Zara-Yaqob ena Hatata Wolde-Hiwot* (4th ed). Addis Ababa.

Daniel Worku. *Ye Ethiopia Filsefina: Hatata Zara-Yaqob ena Metsehafa Chewata Sigawi weMenfesawi*.

Walelign Emiru. (2017). *BeFilsefina Medemem.* Addis Ababa: Bole publishing enterprize

Beauvoir, S.D. (1972). *The Second Sex*. London: Penguin.

Mill, J. S. (1984). The Collected Works of John Stuart Mill, Volume XXI - Essays on Equality, Law, and Education (J. M. Robson, Ed.). Toronto: University of Toronto Press; Routledge and Kegan Paul. Retrieved April 19, 2019, from http://oll.libertyfund.org/titles/255

Millett, K. (2000). *Sexual Politics*. University of Illinois Press: Illinois.

Russell, B. (1961). *History of Western Philosophy*. London: George Allen and Unwin.

Sergew Hable Sellassie. (1981). *Bookmaking in Ethiopia*. London: Oxford University Press.

Sumner, C. (1998). *African Philosophy.* Seminar Proceedings. Addis Ababa: Addis Ababa University.

Tyson, L. (2006). *Critical Theory Today: A User-Friendly Guide*. Routledge: USA.